## *ተሸብሮ ህዝብን ማሸበር የፖለቲካ ውድቀት ምልክት ነው*
## *(ከኦነግ ኢንፎ ዴስክ)*

*የህወሃት መንግስት በሃገር ቤት ህዝባዊው ተቃውሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለበት መምጣቱን መደበቅ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ስርኣት ከጥቂት ኣመታት በፊት ይነዛ የነበረውና ዛሬ የተያያዘው ፕሮፓጋንዳ በእጅጉ ይቃረናል። ቀደም ሲል የነበረው የወያኔ ፕሮፓጋንዳ እንደ ኦነግ ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ተደምስሰዋል በማለት ህዝብን ተስፋ ለማስቆረጥ በመጣር ላይ ያተከረ ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ተቃዋሚ ድርጅቶቹ ያልተደመሰሱና በይፋ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ከማመኑም ባሻገር የእንቅስቃሴኣቸው ስፋት በእጅጉ ስጋት ላይ የጣለው መሆኑን መሸሸግ ተስኖታል። እነዚህን ተቃዋሚ ሃይሎች ህዝቡ እንዳይደግፋቸው ለማስፈራራት መሰረተ ቢስ ዶክሜንታሪ ፊልሞችን እያቀነባበረ የቁራ ጩሄት መጮህን እንዳማራጭ ወስዷል።*

*የስርኣቱ ካድሬዎች ጥርቅም በሆነው ፓርላማ ተብዬ ፀደቀ በተባለው የውንጀላ ህግ መሰረት የኣሸባሪነት ጥላሸት የተቀቡት ሃገር በቀል የፖለቲካ ድርጅቶች ኦነግ፣ ኦብነግና ግንቦት7 ናቸው። የሚገርመው ደግሞ ወያኔ እነዚህን የፖለቲካ ድርጅቶች በኣሸባሪነት ሲወነጅል በሃያላን መንግስታት ዘንድ በሽብርተኛነት የተፈረጁትን እንደ ኣልቃይዳና ኣልሸባብ ያሉትን ኣክራሪ ሃይሎችንም ኣክሎበት የክሱን ይዘት ወደ ኣለማቀፋዊ ደረጃ ከፍ ለማድረግ መጣሩ ነው። ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ሲል እያወቀ በምናቸውም ከቶ የማይመሳሰሉ የውስጥና የውጭ ሃይሎችን ኣንድ ላይ በርዞ ለማቅረብ ሞከረ። ይሁንና የኣለም ሃያላን መንግስታት ወያኔ የሃገር ቤት የፖለቲካ ድርጅቶችን እንደ ኣልቃይዳ ካሉ ሃይሎች ጋር ኣንድ ላይ መደመሩን ስቀውበት በቀላሉ ሳይቀበሉት ኣለፉ። ለምን ቢባል ሶስቱም ሃይሎች፣ ማለትም ኦነግ፣ ኦብነግና ግንቦት7 ከወያኔ ስርኣት ጋር በሰላማዊ መንገድ የመታገል እድል ስለተዘጋባቸው በተቻላቸው የትግል ስልት ሁሉ ስርኣቱን ለመፋለም የተገደዱ ሃይሎች መሆናቸውን ምእራባውያኑ ስለማይስቱት ነው።*

*ወያኔ እንደ ኣንጋፋ ደመኛ ጠላቱ ኣምርሮ የሚወነጅለውን ድርጅታችን ኦነግን እንመልከት። ግንባሩ የደርግ ስርኣት ተገርስሶ የሽግግር መንግስቱ በተመሰረተ ማግስት ከሰላማዊው የትግል ጎዳና በወያኔዎቹ ተፅእኖ ተገፍቶ የወጣ ድርጅት ነው። ከወያኔ ጋር በሰላማዊ መንገድ ታግሎ የቆሙለትን ህዝብ መብትና ጥቅም ማስከበር ከቶ የማይታሰብና ወያኔ ኦሮሞን ጨምሮ የሁሉም የሃገሪቷ ህዝቦች ጠላት መሆኑን ገና በጠዋቱ የደረሰበት ድርጅት በኢትዮጵያ ቢኖር ኦነግ ነው። ኦብነግም በበኩሉ የህወሃት መንግስት ለኦጋዴን ህዝብ ያለውን ጠላትነት ከማረጋገጡ የተነሳ እንዲህ ካለው ፀረ ህዝብ መንግስት ጋር ኣብሮ መስራት የማይቻል መሆኑን ተገንዝቦ የቆመለትን ህዝብም ማስገንዘቡ እሙን ነው። በተመሳሳይ መልኩ የግንቦት7 ንቅናቄም በቅንጅት ፓርቲ ኣባልነት በ1997ቱ ምርጫ ላይ በተሳተፈ ማግስት ኦነግ ከ1984 ጀምሮ ሲያስገነዝብ የቆየውን ከለበሰው የበግ ለምድ ስር የተደበቀውን እውነተኛው የወያኔ ማንነት ደረሰበት። እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ ይህ የወያኔ ኣስመሳይነት የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርበት ለሚከታተል ለየትኛውም ወገን ግልፅ እየሆነ መጥቷል።*

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በነገሰው ኣምባገነናዊ ስርኣት ሳቢያ ሰላማዊው የትግል ስልት ከቶ የማይታሰብ መሆኑ ከምን ጊዜውም በላይ ተረጋግጧል። በተለያዩ ጊዜያት ከስርኣቱ ጋር በሰላማዊ መንገድ ለመስራት የሞከሩ ንቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ መጨረሻቸው ኣንድም መፈራረስ፣ መሪዎቻቸው መታሰር፣ መገደል ኣልያም ሃገር ጥለው ለስደት መዳረግ ሆነ። ከነዚህ ኣደጋዎች የተረፉ ቢኖሩ ትርጉም ያለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከማድረግ ተገትተው ሽባ ሆነው ለመኖር ተገደዱ። በዝምታ ተሸብበው ቢቀመጡም ደግሞ በየጊዜው በስርኣቱ የሚወርድባቸው የማስፈራሪያ ጋጋታ ኣይቀርላቸውም።

እንዲህ ያለው የወያኔ ውሃ ቀጠነ ጣጣ ሰላማዊውን የትግል ሜዳ የሚያሰፋ ሳይሆን ነፃ ህልውና ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሙሉ ሌሎች የትግል ኣማራጮችን እንዲፈትሹ የሚያስገድድ ነው። በመሰረቱ የፖለቲካውንና የትጥቁን የትግል ስልቶች ኣጣምሮ መንቀሳቀስ ሽብርተኛነት ሳይሆን ወያኔን የሚፋለሙበት ብቸኛው የትግል ስልት ሆኗል። ይህን ያደረገው ደግሞ ወያኔው ራሱ ነው። ከ20 ኣመታት በፊት ኦነግን የገጠመው እንዲህ ያለው እንቅፋት ዛሬ ቀስ በቀስ ድርጅታዊ ነፃነት ያላቸውን ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ሲያዳርስ እያየን ነው። በዚህ ኣይነቱ የፖለቲካ ኣረንቋዋ ውስጥ በተዘፈቀች ሃገር የኣብዛኛውን ዜጋ ህይወት የሚያሻሽል ሰላምና ልማት ከቶ ኣይታሰብም። ከወያኔው ዘረኛና የለየለት ኣምባገነናዊ ስርኣት ተስፋ ቆርጦ የፖለቲካና የትጥቅ ትግል ኣጣምሮ ለመንቀሳቀስ የተገደደ ሃይል ሁሉ ሽብርተኛ የሚባል ከሆነ ጭቆናና ኣንገሽግሾት ትግል የናፈቀው የሃገሪቷ ዜጋ ሁሉ ሽብርተኛ ሆነ ማለት ነው። ለምን ቢባል ዛሬ በኢትዮጵያ ጭቆናና የመረረው ዜጋ የተቃዋሚ ድርጅት ኣባል ወይም ደጋፊ ብቻ ሳይሆን መላው ህዝቡ ነውና።

ወያኔ ዘንድ የሽብርተኛነት ጥላሸት የተቀቡት ሶስቱ ድርጅቶች የስርኣቱን ኣምባገነናዊና ፋሺስታዊ ፖሊሲ የተገነዘቡና ከሰላማዊው የትግል ጎዳና ተገፍተው የወጡ ናቸው። ስርኣቱም የድርጅቶቹን ጥንካሬና ከበስተጀርባቸው የተሰለፈውን ግዙፍ ህዝባዊ ድጋፍ ስለሚረዳ ሰላማዊ እንቅልፍ ተኝቶ ማደር ኣልቻለም። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የድርጅቶቹን እንቅስቃሴ ከጎሮቤት ሃገር ጉዳይ ጋር ማቆራኘቱም ተስፋ የመቁረጥና የፍራቻ ምልክት ነው። ኦነግም ሆነ በስም የተጠቀሱት ሁለቱ ድርጅቶች በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ለቆሙላቸው ህዝቦች ከመታገል በቀር ወያኔ እንደሚከሰው ከጎሮቤት ሃገር ኤርትራ ጋር ኣንድ ላይ የሚያቆራኛቸው ጉዳይ የለም።

የወያኔ መንግስት ስለኦነግ ባነሳ ቁጥር የኤርትራን ስም ሳያነሳ ያለፈበት ጊዜ የለም። ኦነግ ኤርትራ ውስጥ ተመስርቶ ወደ ኢትዮጵያ የገባ እስኪመስል ድረስ ያማርራል፣ ይከሳል። የኦነግ እንቅስቃሴ ባስደነበረው ቁጥር "ኤርትራ ነች የላከችብን" እያለ ራሱ ሳይቀር ኣሳምሮ የሚያውቀውን ሃቅ ሊያዛባ በከንቱ ይደክማል። ኦነግ ውልደቱም፣ መሰረቱም እንቅስቃሴውም እዚያው ኦፍንጫው ስር መሆኑን ግን ልቡ ኣሳምሮ ያውቀዋል። የዚህ ኣይነቱ ቅጥፈታዊ ኣቀራረብ ሁለት ኣላማዎች ያሉት ይመስላል። ባንድ በኩል ኦነግንም ሆነ የድርጅቱ ደጋፊ የሆነውን ሰፊውን የኦሮሞ ህዝብ እንደመናቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ኦነግ

ጠላቴ ከሆነች ሃገር ጋር ጥምረት ፈጥሮ ተነስቶብኛልና አውግዙልኝ ብሎ እንደመማፀን አልያም እንደማስፈራራት ይመስላል።

ድፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከሆነ ኦነግ ኤርትራን ነፃ አውጥቶ ዛሬ እንደመንግስት በመምራት ላይ ካለው የኤርትራ መሪ ድርጅት ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ግንኙነት የጀመረው ገና ከፀረ ደርግ ትግሉ ወቅት አንስቶ ነበር። ይህን ደግሞ ራሱ ከወያኔ የበለጠ በቅርበት የሚያውቅ አካል የለም። እንዲህ ያለው የፖለቲካ ግንኙነት በአለማችን ላይ በማናኛቸውም ጉርብትና ባላቸው ሃገሮች ወይም ህዝቦች መካከል ሊፈጠር የሚችል ክስተት ነው። ይህ ድፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዛሬ ወያኔ ከኤርትራ መንግስት ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋዋረጠና እሱን ተከትሎ የሚቋዋረጥ አይሆንም። ኦነግ በሁለት እግሮቹ ራሱን ችሎ የቆመ፤ የተመሰረተለትን ህዝባዊ አላማ በነፃነት የሚያራምድ ነፃ ድርጅት እንጂ የወያኔ ህወሃት ተለጣፊ ቡድን አይደለም። ኦነግ ማለት በወያኔ አዛዥነት ቁጭ ብድግ ከሚሉት ፒዲኦዎቹ መካከል አንዱ አይደለም። ስለሆነም ወያኔ ያወገዘውን አውግዞለት ወያኔ የደገፈውን መደገፍ የኦነግ ጉዳይ አይደለም። የራሱን ድርጅታዊ ህልውና ጠብቆ ለአስርት አመታት መራራ መስዋእትነቶችን እየከፈለ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ያለው ክብርና ድጋፍ ሳይለየው በፍትሃዊ ትግሉ የዘለቀ ነፃ ድርጅት ነው። ስለሆነም ኦነግ ከማናቸውም መንግስታትም ሆነ ድርጅቶች ጋር የድፕሎማሲ ግንኙነት ለመፍጠርም ሆነ ለማቋዋረጥ ከወያኔ ፈቃድ አይጠይቅም። ይህንን ደግሞ ወያኔም ራሱ አሳምሮ ያውቃል።

ዛሬ የወያኔ መንግስት ሚድያዎች ከማናቸውም ጊዜ በተለየ መልኩ በፀረ ኦነግና መሰሎቹ ፕሮፓጋንዳ ተጠምደዋል። ይህም ስርኣቱ በተቃዋሚ ድርጅቶች በተለይም በኦነግና ቄሮው የኦሮሞ ወጣት እንቅስቃሴ ሳቢያ ክፉኛ ስጋት የገባው መሆኑን ያሳያል። ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ሶሶቱን ታጋይ ድርጅቶች ለመወንጀል ያለሙ ርካሽ ዶኪሜንተሪ ፊልሞቹን በተከታታይ በሚድያዎቹ በመልቀቅ ምን ያህል ተሸብሮ ህዝብን ሊያሸብር እንደተነሳ በራሱ ላይ እየመሰከረ ነው። ለምሳሌ *ኣኬልዳማ* ብሎ የሰየመውን አሰልቺ ተከታታይ የውንጀላ ዶኪሜንተሪውን “ከ13 አመት በታች የሆኑ ህፃናት እንዲከታተሉት አይፈቀድም” ማለቱ በሽብርተኛነት የሚከሳቸውን ሶሶቱን ድርጅቶች ምን ያህል በአስፈሪ ጭራቅነት መስሎ ህዝብን ለማሸበር ደፋ ቀና የሚል ቡድን መሆኑን በገሃድ ያሳያል።

ወያኔ ለምን ይህን ያህል ተሸብሮ ህዝብን ለማሸበር ተነሳ የሚለው ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ ይሻል። የጥያቄው ምላሽም በሁለት ተያያዥ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። የመጀመሪያው፤ የተቃዋሚው ሃይል ትግል እንደ ሰደድ እሳት ስርኣቱን ቀለበት ውስጥ አስገብቶ ቀስ በቀስ ሊውጠው እየተቃረበ መሆኑን በመረዳቱ የሚያሳየው የመንፈራገጥ ምልክት ሊሆን ይችላል። ሁለተኛውና ተያያዥ ምላሽ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ወያኔ የብዙሃን ህዝቦች ድጋፍ የሌለው አናሳ ቡድን በመሆኑ ራሱ የተሸበረውን ያህል ተስፋ ያጣባቸውን ህዝቦች ማሸበር እንደብቸኛ አማራጭ ታይቶት ሊሆን ይችላል። በተቃዋሚ ሃይሎቹ ትግል በስጋት ተውጦ እንደ ቡድን በግሉ መሸበሩ ተገቢ ነው። ነገር ግን ህዝቦች ከወያኔ ጋር የሚሸበሩበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ወያኔ በጭራቅነት መስሎአቸው

ህዝቦችን ሊያስፈራራ የሚሞክርባቸው ድርጅቶች ከህዝቦቹ ኣብራክ የወጡና ለህዝቦቹ መብቶች መረጋገጥ የሚታገሉ ናቸውና።

እኔ ልማታዊ መንግስት ስሆን ተቃዋሚዎች ግን ኣላማቸው እኔ የማለማውን ልማት ማጨናገፍ ነውና ከጎኔ ቆማችሁ ተቃዋሚዎቹን ኣውግዙልኝ ብሎ ቢጮህም የጠበቀውን ውጤት ከህዝቡ ባለማግኘቱ ወያኔ ክፉኛ የተበሳጨ ይመስላል። የሃገሪቷ ህዝቦች እንደሆን ነገሩ እንግዳ ኣይሆንባቸውም። በጠመንጃ ኣፈሙዝ ስር ስለታፈኑ የሚያምኑበትን ነገር መናገር ቢሳናቸውም የወያኔን ቀጣፊነት ከተረዱ ሰነባብተዋል። በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ዋነኛው የወያኔ ኣረመኔያዊ ጥቃት ሰለባ እንደመሆኑ መጠን በጭራቅነት ተመስሎ መታየት የሚገባው ኦነግ ወይም ሌሎች መሰል ታጋይ ድርጅቶች ሳይሆኑ ራሱ ወያኔ ስለመሆኑ እርግጠኛ ነው።

የህወሃት መንግስት ተቃዋሚዎቹን ኣሳጣለሁ ብሎ የተያያዘውን የቀቢፀ ተስፋነት ፕሮፓጋንዳ በቀጠለ ልክ በህዝብ ዘንድ ይበልጥ እየተጠላና እየተነጠለ መሄዱ ኣይቀሬ መሆኑ የገባው ኣይመስልም። ለራሱ ተሸብሮ ሰላማዊውን ህዝብ በማሸበር የፖለቲካ ድጋፍ ማግኘት የማይታሰብ ነው። እንዲህ ያለው ኣካሄድ የፖለቲካ ውድቀት ምልክት መሆኑም መታወቅ ኣለበት። እንደገና ሊሰመርበት የሚገባው ነጥብ ወያኔና የሃገሪቷ ህዝቦች ማለት ሆድና ጀርባ ናቸው ብለናል። ወያኔን የሚያሸብረው እንቅስቃሴ ለህዝቦቹ የምስራች ዜና እንጂ ኣስደንጋጭ መርዶ ኣይሆንም። ወያኔ በገዛ ጠላታዊ ተግባሩ ውጤት ስለተሸበረ ብቻ ነፃ ህዝቦች ከርሱ ጋር የሚሸበሩበት ኣንድም ምክንያት ኣይኖርም። ወያኔን ኣስደንብሮ ሽብር እየለቀቀበት የሚገኘው ህዝባዊው ትግል ህዝቦቹ ከፋሺስታዊው ስርኣት መንጋጋ ስር እስከሚወጡ ድረስ ተጠናክሮ ይቀጥላል!

ፍትህ ያሸንፋል!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ